Paid Leave Oregon

# ጥቅማ ጥቅሞች

## በኦሪጎን ውስጥ ያሉ ተቀጣሪዎች ቤተሰቦቻችን፣ ጤናችን እና ደህንነታችን ላይ ተፅዕኖ ለሚያሳድሩ አንዳንድ የህይወት ወሳኝ ጊዜያት ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ እንዲወስዱ የሚያስችል አዲስ ፕሮግራም።

**የቤተሰብ ፈቃድ –** ከባድ ህመም ወይም ጉዳት ላጋጠመው የቤተሰብ አባል እንክብካቤ ለማድረግ ወይም ከወሊድ፣ ጉዲፈቻ ወይም የማደጎ እንክብካቤ ምደባ በኋላ ከአዲስ ህፃን ጋር ለመላመድ።

**የሕመም ፈቃድ –** አንድ ሰው ከባድ የጤና ችግር በሚያጋጥመው ጊዜ።

**የደህንነት ፈቃድ –** ለጾታዊ ጥቃት፣ የቤት ውስጥ ጥቃት፣ ትንኮሳ ወይም የማሳደድ ተጠቂዎች።

**የቤተሰቤ አባል ቢታመም ወይም ቢጎዳ ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ ጥቅማ ጥቅሞችን መጠቀም እችላለሁ?** አዎ። የታመመ ወይም የተጎዳ የቤተሰብ አባልን ለመንከባከብ ሽፋን አለዎት።

**ከክፍያ ጋር በሚሰጥ ፈቃድ ፕሮግራም ስር የቤተሰቤ አባል ተደርጎ የሚቆጠረው ማነው?** የስጋ ዝምድና ያለው ወይም ከእርስዎ ጋር ያለው ግንኙነት እንደ ቤተሰብ የሆነ ማንኛውም ሰው።

**ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት መቼ ማመልከት እችላለሁ?** ሴፕቴምበር 2023።

**መውሰድ የምችለው ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ ስንት ነው?** በአመት 12 ሳምንት ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ፣ እና ከእርግዝና ጋር ለተያያዙ የጤና እክሎች ተጨማሪ ሁለት ሳምንታት። ከክፍያ ጋር የሚሰጥን ፈቃድ በተለያየ ጊዜ አንድ አንድ ወይም በተከታታይ መውሰድ ይችላሉ።

**ማግኘት የምችለው ገንዘብ ስንት ነው?** አብዛኞቹ ሰራተኞች የደመወዛቸው 100% ይተካላቸዋል። የጥቅማ ጥቅምዎ መጠን የሚመሰረተው ባለፈው ዓመት ባገኙት አማካይ ደመወዞች ላይ ነው። ዝቅተኛው ሳምንታዊ ጥቅማ ጥቅም ወደ $57 □□□ ይሆናል እና ከፍተኛው ሳምንታዊ ጥቅማ ጥቅም ደግሞ ወደ $57 □□ ከፍተኛው ሳምንታዊ ጥቅማ ጥቅም $1,375 ይጠጋል።

**ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ ጥቅማ ጥቅሞችን ለመቀበል መስፈርቶቹ ምንድን ናቸው?** ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ ጥቅማ ጥቅሞችን የሚጠይቁ ሰራተኞች የሚከተሉትን ማሟላት አለባቸው፦

- ብቁ የሚያደርግ ክስተት ያጋጠማቸው ሊሆኑ ይገባል
- ማመልከቻ ማጠናቀቅ አለባቸው
- ባለፈው ዓመት ውስጥ ያገኙት ደመወዝ $1,000 መሆን አለበት
- ከደመወዛቸው ላይ በሚደረግ ተቆራጭ አማካይነት ከክፍያ ጋር ለሚሰጥ ፈቃድ ትረስት ፈንድ መዋጮ ማድረግ አለባቸው

## ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ ለመውሰድ ማሰቤን ለአሰሪዬ ማሳወቅ ያለብኝ መቼ ነው?

ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ መውሰድ እንዳለብዎት ካወቁ፣ ፈቃድ ከመውጣትዎ ቢያንስ 30 ቀናት በፊት ለአሰሪዎ በጽሑፍ ማሳወቅ አለብዎ። ባልተጠበቀ ሁኔታ ፈቃድ መውሰድ ከፈለጉ፣ ፈቃድዎን በጀመሩ በ24 ሰዓት ውስጥ የቃል ማሳወቂያ መስጠትና ፈቃድዎን በጀመሩ በሶስት ቀናት ውስጥ የጽሑፍ ማሳወቂያ መስጠት አለብዎት።

## ከክፍያ ጋር የሚሰጥ የኦሪጎን ፈቃድ የሚሸፍናቸው ሰራተኞች የትኞቹ ናቸው?

በኦሪጎን ውስጥ የሚሰሩ አብዛኞቹ ሰራተኞች ከክፍያ ጋር በሚሰጥ ፈቃድ ፕሮግራም ይሸፈናሉ። ደመወዝተኛ ሰራተኞች፣ በሰዓት፣ በሙሉ ጊዜ፣ በትርፍ ጊዜ ወይም በተወሰነ ወቅት የሚሰሩ ሰዎች በሙሉ ይሸፈናሉ።

## ከክፍያ ጋር በሚሰጥ የኦሪጎን ፈቃድ የማይሸፈኑት ሰራተኞች የትኞቹ ናቸው?

ከክፍያ ጋር በሚሰጥ ፈቃድ የማይሸፈኑ ሰዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

- የፌዴራል መንግስት ተቀጣሪዎች
- የትራይባል መንግስት ተቀጣሪዎች
- በራሳቸው የግል ስራ የሚተዳደሩ ወይም የግል ስራ ተቋራጮች
- ከኦሪጎን ውጭ ብቻ የሚሰሩ ሰራተኞች

## ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ ሽፋን ብቁ ካልሆንኩ፣ ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ ፕሮግራምን ለመቀላቀል መወሰን እችላለሁ?

ትራይባል መንግስታት ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ ፕሮግራምን ለመቀላቀል መወሰን ይችላሉ፣ ሰራተኞቻቸውም ሽፋን ይሰጣቸዋል። በራሳቸው የግል
ስራ የሚተዳደሩ ወይም የግል ኮንትራክተሮችም ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ ፕሮግራምን ለመቀላቀል መወሰን ይችላሉ።

## የኦሪጎን ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ ፕሮግራም ከFamily Medical Leave Act (FMLA) እና ከOregon Family Leave Act (OFLA) የሚለየው እንዴት ነው?

ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ ፕሮግራም እና FMLA/OFLA መካከል ያሉት አንዳንድ ልዩነቶች ከዚህ በታች ያለው ማጠቃለያ ነው። እያንዳንዱ ፕሮግራም በርካታ ደንቦች ያሉት ሲሆን ውስብስብ ሊሆን ይችላል። ለእርስዎ ፍላጎት የበለጠ ተስማሚ የሆነው ፕሮግራም የትኛው እንደሆነ ለመወሰን፣ እባክዎ ከሰው ኃይል ተወካይዎ ጋር አብረው ይስሩ።